## ሳያዩ ያመኑ! አይተው የታወሩ!



www.bigstock.com · 282196648

ልብን ሳትከፍሉ ሳታዩ እንድታምኑ፣
መለኮትን ብቻ አምልኩ ቢባሉ፣
የመጣፍ ሕግ ጥሰው ምሁሩ ካህኑ፣
እባብ ሳያዩ አምነው ያዩትም ታውረው፣
ስንቱን አስጨረሱ በመርዝ አስነድፈው፡፡

ሕዝብን ሰላም ነስቶ ሲያሰቃይ የኖረው፣
በክርስቶስ ፋንታ ጲላጦስ የፈታው፣
የሳጥናኤል አሽከር በርባን የተባለው፣
በሉ ተከተሉኝ መሲህ ነኝ ሲላቸው፣
አምነው ተቀበሉት ተእግሩ ሥር ተደፍተው፡፡

ተዓይን ተብሌና ጆሯቸውን አምነው፣
የሚያውቁት ይሁዳ መሲህ ነኝ ሲላቸው፣
ጭራሽ ሳያቅማማሙ አምነው ተከትለው፣
ሕዝቡን አሳሳቱት የምሁር ካድሬ ሆነው፡፡

የፈርኦን አብራክ ብቅ ሲል እያዩ፣
ዓይናቸውን ቀርቶ ጆሯቸውን ያመኑ፣
ባህር የሚያሻግር ሙሴ መጣ እያሉ፣
በአገር ውስጥ በውጪም ጮቤ የደነሱ፣
ሕዝብን አደናብረው ተገደል ከተቱ፡፡

በሥራው ይመዘን የሰው ልጅ ቢባሉ፣
በስብከት ከረጢት ሰባኪ እየለኩ፣
ሕዝብን አስጨርሰው እግዜርን አስከፉ፡፡

ሳያዩ ያመኑ አይተው የታወሩ፣
የፈርኦን ጆሌን ሙሴ መጣ እያሉ፣
ላንቃቸው እስቲደርቅ ውሸት የሰበኩ፣
ጠልሰሞች ጠልስመው ሕዝብን ያሳሳቱ፣

ከንስሃ ደጃፍ እጅግ ስለራቁ፣
በኩነኔ መንገድ እንደተጓዙ አሉ፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሚያዚያ ሁለት ሺ አስራ አራት ዓ.ም.